ከሙስና የጸዱች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ–ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 45 ሀምሌ 15/2018 ዓ.ም


## በውስጥ ገጾች


ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በቁጥጥር ስራዎች የላቀ ውጤት ማስመዝገቡን አስታወቀ

ገጽ-2

ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር እንደሚገባ የህግና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስታወቀ

ገጽ-3

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እስከ ከፍተኛ ባለስልጣናት የሀብት ምዝገባ ያለው የፖለቲካ ቁርጠኝነት!

ገጽ-5


**የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካለዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ ባሉበት ሁነው ይጠቁሙ!**

## በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ ታወር ግንባታ ግዥ የጨረታ ሂደት ላይ ምክረ ሀሳብ ቀረበ



በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ(ATC) ታወር ግንባታ

ግዥ የጨረታ ሂደት ላይ የፌደራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት በማካሄድ ምክረ ሀሳብ አቅርቧል። ኮሚሽኑ በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት ሙስና ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ሲጠረጥር ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት አስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት በማካሄድ ሂደቱ እንዲቋረጥ የማድረግ ስልጣን አለው።

በዚህም፣ መሠረት በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን በያቤሎ በደብረማርቆስ እና በሚዛን አማን ኤርፖርት የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ(ATC) ታወር ግንባታ ግልጽ ጨረታ ሂደት ላይ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት በማካሄድ ምክረ ሀሳብ አቅርቧል።

ወደ ገጽ-2 የዞረ

## ከተማ አስተዳድሩ ሌብነትና ሙስናን ለመታገል በቁርጠኝነት እየሰራ ነው - ከንቲባ አዳነች አቤቤ

የከተማ አስተዳደሩ ሌብነትንና ብልሹ አሰራርን በተጨባጭ ለመታገል በቁርጠኝነት እየሰራ ነዉ፡ ፡ በዚሁ መሰረት የተለያዩ ጥፋቶችን በመፈጸሙ 5ሺህ 857 አካላት ከነዚህ መካከል 79 ሹመኛ አመራሮች፣ 213 የሜሪት አመራሮች፣ 5 ሺህ 430 ባለሙያዎች እና 135 ተገልጋዮች እንደ ጥፋታቸው ክብደት ከማስጠንቀቂያ እስከ ስንብትና በህግ ተጠያቂ እስከማድረግ የሚደርሱ እርምጃዎች ተወስደዋል።
በአመራሩ ዘንድ በሚታዩ የሪፖርት ግድፈቶችና የመረጃ አያያዝ ክፍተቶች ላይ ጠንከር ያለ ትችት የሰነዘሩት



ከንቲባዋ፣ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ማቅረብ ከሌብነት ጋር በተመሳሳይ ደረጃ የሚያስጠይቅ እንደሆነ በማስጠንቀቅ ወደፊት የሚቀርቡ



ሪፖርቶች በሕዝቡ ሕይወት ላይ ያመጡትን ሁለንተናዊ ለውጥና ጥቅም በግልጽ ማሳየት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

## የኮሚሽኑ አመራሮች እና ሠራተኞች የደም ልገሳ መርሐ ግብር አካሄዱ



የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች እና ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት ደም ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች የደም ልገሳ ኘሮግራም አካሂደዋል። መርሃ ግብሩ፣ ኮሚሽኑ በየዓመቱ የሚያካሂደው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት አንዱ ተግባር ሲሆን፣በህክምና ተቋማት ውስጥ የሚስተዋለውን የደም አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍና

ወደ ገጽ-3 የዞረ

# ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በቁጥጥር ስራዎች የላቀ ውጤት ማስመዝገቡን አስታወቀ



የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በ2018 በጀት ዓመት ባከናወናቸው ዘርፈ-ብዙ የክትትልና የድንበር ቁጥጥር ስራዎች ብልሹ አሰራርን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገቡን ይፋ አደረገ። ተቋሙ የአገልግሎት አሰጣጡን ግልጽና ከሙስና የጠራ ለማድረግ ከሐምሌ 15 ቀን ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል የኤሌክትሮኒክስ ፓስፖርት (e-Passport) አሰራር መሸጋገሩንም ገልጿል።

የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ሰላማዊት ዳዊት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳመለከቱት፤ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ የደህንነት ክፍተቶችንና ህገ-ወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል በተደረገ የተቀናጀ ክትትል የላቀ ውጤት ተመዝግቧል። በበጀት ዓመቱ በተከናወኑ ጥብቅ የክትትል ስራዎች ህገ-ወጥነትንና የህግ የበላይነትን የመናድ ሙከራዎችን ማክሸፍ መቻሉን ዋና ዳይሬክተሯ ገልጸዋል። በዚህም መሠረት፦ የሰነድ ማጭበርበር መከላከል በተቋሙ ልዩ የክትትል ስራ አማካኝነት ሐሰተኛ ሰነዶችን በመጠቀም መታወቂያና ፓስፖርት ለመውሰድ የሞከሩ 4,883 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ውለው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ተደርጓል። ህገ-ወጥ ድንበር መሻገር በየብስና በባህር በር መግቢያዎች በኩል በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር ለመሻገር የሞከሩ 55,013 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ውለዋል። ይህ እርምጃ በተቋሙ ውስጥ የሚፈጸሙ የሙስና እና የደላላ ሰንሰለቶችን ለመበጠስ እንዲሁም የሀገርን ደህንነት ለማስጠበቅ ትልቅ ሚና እንዳለው ተመልክቷል። ተቋሙ በበጀት ዓመቱ የአሰራር ክፍተቶችን በመድፈንና የአገልግሎት ተደራሽነትን በማስፋት ከፍተኛ የፋይናንስ ስኬት አስመዝግቧል። በአጠቃላይ ገቢ፦ 42.7 ቢሊዮን ብር የተሰበሰበ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 5.4 ቢሊዮን ብሩ በውጭ ምንዛሬ የተገኘ ነው። የቅርንጫፎች መስፋፋት ቀደም ሲል ከነበሩት 12 የፓስፖርት አገልግሎት ቅርንጫፎች ቁጥር ወደ 23 በማሳደግ የአገልግሎት አሰጣጡን ፍትሐዊና ተደራሽ ማድረግ ተችሏል።

# የስነምግባር ትምህርት መደጋገም ያስፈልጋል ተባለ

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከዳሽን ባንክ ጋር ”የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት በፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ‘ በሚል መሪ ርዕስ በተካሄደው ሥልጠና ላይ ከ550 በላይ የባንኩ ዲስትሪክት ባንክ ማኔጀሮች፣ ኦፐሬሽን ማኔጀሮች፣ የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች እና የኤች አር (HR) ፓርትነሮች ተሳትፈዋል። የሥልጠናውን መርሃ-ግብር በንግግር የከፈቱት የዳሽን ባንክ የስነምግባርና ኮንዳክት መምሪያ ዳይሬክተር አቶ ጥላዬ እንየው፣ የስነ-ምግባር ትምህርት በተደጋጋሚ መሰጠት ያለበት ጉዳይ መሆኑን አሳስበዋል። ዳይሬክተሩ በንግግራቸው፦”የስነምግባር ትምህርት መደጋገም ያስፈልገዋል፤ ምክንያቱም የስነምግባር ሥልጠና ማወቅን ሳይሆን መሆንን ይጠይቃልና!” ሲሉ የሥልጠናውን አስፈላጊነትና የአመራሩን ሚና ገልጸዋል።

የሥልጠናው ዋነኛ ግብ የንድፈ-ሀሳብ ትርጉም ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን፣ በአመራሩ ዘንድ ተግባራዊ የባህሪ ለውጥ ማምጣትና ከጥቅም ግጭት የፀዳ ተቋማዊ ውሳኔ አሰጣጥን ማጎልበት መሆኑም ተመላክቷል። በመሆኑም ሥልጠናው የከፍተኛ አመራሩን ደረጃና ብቃት እንዲመጥን ለማድረግ ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጎበት የተዘጋጀ መሆኑ ተገልጿል። በዕለቱ በምሁራኑ በሰፊው የተብራራው የጥቅም ግጭት ጉዳይ ሲሆን፣ ይህም በግል ፍላጎት እና በመንግሥት/በሕዝብ ጥቅምና ኃላፊነት መካከል የሚፈጠር አለመጣጣም መሆኑ ተብራርቷል። ስነ-ምግባራዊ መሆን አመራሩ ከግለኝነት ስሜት ወጥቶ፣ ከሙስናና ከብልሹ አሠራር የፀዳ ውሳኔ እንዲወስን እንደሚያግዘው ተገልጿል።

ውሳኔ የመሪዎች የዕለት ተዕለት ተግባር ቢሆንም፣ ውሳኔዎች ትክክለኛ፣ የተሳሳቱ፣ አድልዎ ያለባቸው፣ ሰዎችን ለመጉዳት ወይም ለግል ጥቅም የሚደረጉ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተጠቁሟል። ውሳኔ በስነ-ምግባር ላይ ሲመሠረት ግን ጥቅሞች እንደሚያስገኝ ተመልክቷል። ከጥቅሞቹ መካከል ከህሊና ፀፀትና ወቀሳ መታደግ፣ እፎይታንና ሰላምን መስጠት፣ አላስፈላጊ ወጪን መቆጠብና መልካም አስተዳደርን ማስፈን፣ ከተጠያቂነት ማዳንና የተቋምን ዕድገት ማፋጠን ነው። ይህንን ከፍተኛ ጥንቃቄ የተደረገበትን ሥልጠና ዶ/ር ተስፋዬ ሂርጳሳ፣ ዶ/ር ዮሐንስ ጴጥሮስ እና ዶ/ር አወቀ አሸናፊ በጋራ በመሆን የመሩት ሲሆን፣ ከኮሚሽኑ የተወከሉት አቶ ኪዳነ ምህረትም በዕለቱ ተገኝተዋል።








## በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ

ከገጽ-1 የዞረ

በግዥ ሂደቱ፣ ለአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ (ATC) ማማዎቹ ግንባታ ግልጽ ጨረታ አየር ላይ የቆየባቸው ቀናት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ጨረታ በአየር ላይ የመቆየት ጊዜን የመወሰን ኃላፊነት ያለው ቢሆንም ሰፊ ተወዳዳሪዎችን ከመሳብ አንጻር የቆይታ ጊዜው ቢሰፋ የተሻለ አማራጭ ያሰፋል የሚልና በሌሎች የክልል ከተሞች የተገነቡና በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ የታወር ግንባታዎች የጥራት ችግር አላስፈላጊ የጊዜ መጓተት መንግስትን ለተጨማሪ ወጪና የጊዜ ብክነት የዳረጉ መሆኑ በጥናት ግኝቱ የተመላከተ ነው። በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋዉና የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አቶ ደንጌ ቦሩ፣ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ዋና ዳሬክተር አቶ ዮሃንስ አበራ

እና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት የግዥ ጨረታ ሂደቱና አፈጻጸሙ የጥናት ግኝትና ምክረ ሀሳብ ሪፖርት ቀርቦ ዉይይት የተደረገ ሲሆን፣ በቀረቡት ግኝቶችና ምክረ ሀሳቦች መግባባት ላይ ተደርሷል።

በቀጣይ በተቋሙ የሚከናወኑ የግዥ ሂደቶች ከሙስና እና ብልሹ አሠራር የጸዱ ሆነው እንዲፈጸሙ የሚያስችል ምክረ-



ሐሳብ ተሰጥቷል። በተለይ በአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ(ATC) ታወር ሥራ ላይ የሚስተዋሉ የጥራትና በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ አለመጠናቀቅ ችግሮችን አመራሩ በየጊዜው ክትትል ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተመላክቷል፡ ፡ ለአብነት የአሶሳ፣ የጋምቤላና የሰመራ ታወር ግንባታ ተጠቃሽ መሆናቸው ተጠቁሟል።

# ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር እንደሚገባ የህግና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስታወቀ





በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህግና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ የ2018 በጀት ዓመት ሁለተኛ ግማሽ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ገምግሟል። በመድረኩ የተገኙት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ተወካይ አቶ ግርማ ጊቻሞ በክልሉ ተቋማትን በዲጂታል ቴክኖሎጂ በማዘመን የብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመፍታት የተደረገው ጥረት ውጤት እያመጣ ነው ብለዋል። ኮሚሽኑ 336 ሚሊዮን በላይ የሚገመት ብር በቅድመ መከላከል እንዲሁም ተመዝብሮ የነበረውን የህዝብ እና የመንግስት ሀብት ማዳን መቻሉ አበረታች መሆኑንም ተናግረዋል። የሥነምግባር ባለሙያዎችን አቅም በማሳደግ ተጠያቂነት ማስፈን ላይ አሰራሩን ማጠናከር ተገቢ ነው፤ የተቋም አሰራር ወጥነትና ተቀራራቢነት እስከታችኛው መዋቅር ድረስ መጠናከር እንዳለበት ገልፀዋል። የሀገር ኢኮኖሚያዊ ሀብት የሚያወድመውን ሙስናን መታገልና ተጠያቂነት ማስፈን ጠንካራ ትግል የሚጠይቅ ነው፤ ለዚህም ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር ይገባል ብለዋል። ከሀብት ምዝገባ አንፃር ለውጥ መኖሩን አንስተው፣ ባላስመዘገቡት ላይ ተጠያቂነት የማስፈን ሥራው ተጠናክሮ መሠራት እንዳለበት አሳስበዋል። ኮሚሽኑ ሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮች በመፍታት ተጠያቂነትን በማስፈን የህዝብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የጀመረውን ተግባር አጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል። የኮሚሽኑ ኮሚሽነር አቶ ማሞ ቴጋ በበኩላቸው ተቋማዊ የሙስናና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስችል አሰራር ስርዓት ለመዘርጋት በቅንጅት እየተሰራ ነው። ኮሚሽኑ ከመከላከል ባለፈ የሙስና ወንጀል ሲፈፀም ክትትል በማድረግ ለፍትህ አካላት የማሳወቅ ስራ እየሰራ መሆኑን ገልፀው፣ የህግ ተጠያቂነት ስራው በሌላ ተቋም የሚፈፀም መሆኑ ውስንነቱን ለማረም በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን አመላክተዋል። የክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ ሀላፊ አቶ ገብሬ ጋጌ የሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ለማረጋገጥ የተጀመረው ስራ በሂደት ላይ ነው። በክልሉ ከ70 ሺ በላይ የትምህርት ማስረጃዎችን በማሰባሰብ በመንግስትና በግል ተቋም ለመፈተሽ ወረፋ ላይ መሆኑን ተናግረዋል።

## የኮሚሽኑ አመራሮች እና ሠራተኞች የደም ልገሳ

ከገጽ-1 የዞረ

አስቸኳይ የህክምና ክትትል ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ፈጣንና አስተማማኝ ህይወት አድን ድጋፍ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። በቀጣይም ሌሎች የክረምት በጎ አድራጎት ተግባራት በተያዘላቸው መርሐ ግብር የሚካሄዱ ይሆናል።





# በፋይናንስ ዘርፉ ሙስናን ለመከላከል የሚያግዝ ስልጠና ለዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ አመራሮች ተሰጠ

የፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከዳይናሚክ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ ጋር በመተባበር ለተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች በስነምግባር ውሳኔ አሰጣጥ፣ የጥቅም ግጭት መከላከል እና ማስወገድ ዙሪያ የተዘጋጀ የግንዛቤ ፈጠራ ስልጠና ሰጥተዋል።







የተቋሙ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ በውቀቱ አላምረው በስልጠናው ወቅት እንደገለጹት፤ ሙስና ለአንድ ተቋም ብቻ የሚሰጥና የሚተው ጉዳይ ሳይሆን ሁሉም ተቋማት በባለቤትነት ስሜት ሊሳተፉበት የሚገባ ነው። አሁን ላይ ለከፍተኛ አመራሩ የተሰጠው ስልጠና ትልቅ ፋይዳ እንዳለው የጠቀሱት ዋና ስራ አስፈጻሚው፣ አመራሮቹ በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች ሁሉ ተገልጋዮችን የማስተማር፣ የማሳወቅና ህብረተሰቡን የማንቃት ኃላፊነት እንዳለባቸው አሳስበዋል። አቶ በውቀቱ አክለውም፦ "አመራሮች ከሙስና ነጻ በመሆን የፀረ-ሙስና አምባሳደር መሆን አለባቸው። በየቅርንጫፎቻቸው ሲሄዱም ይህንን ግንዛቤ ወደ ታች የማውረድን ትልቅ የቤት ስራ ይዘው መሄድ ይኖርባቸዋል፤ ምክንያቱም ያለ አመራሩ ቁርጠኝነት በሚሊዮኖች የሚቆጠረውን ማህበረሰብ መድረስ አይቻልም" ብለዋል።

የተቋሙ የስነ-ምግባር ክትትል ዲቪዥን ማናጀር ወ/ሮ ሸዋዬ አደራ በበኩላቸው፣ የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በግንዛቤ ፈጠራ ስልጠናዎች ላይ ትኩረት አድርጎ ህዝባዊ ድርጅቶችን እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ተደራሽ ማድረጉን አድንቀዋል። ስልጠናው እውቀት ባላቸው የዩኒቨርሲቲ ምሁራን መመራቱ ውጤታማነቱን የላቀ እንዳደረገውም ጠቅሰዋል። ማናጀሯ አያይዘውም፣ ኮሚሽኑ በስልጠና ረገድ የጀመረውን ጠንካራ ትኩረት በሌሎችም ሥየቁጥጥር፣ የክትትልና የድጋፍ ስራዎች ላይ ከአሁኑ በበለጠ አጠናክሮ ሊቀጥልበት እንደሚገባ ጠቁመው፣ ይህ ከተቻለ ሙስናን ከዚህ በተሻለ መልኩ መከላከልና መቆጣጠር እንደሚቻል ገልጸዋል። የስልጠናው አሰልጣኝ ዶ/ር አወቀ አሸናፊ እያንዳንዱ ግለሰብና አመራር ሙስናን መከላከልን ከራሱ መጀመር እንዳለበት አሳስበዋል። በስልጠናው ማጠቃለያ ላይ ከተሳታፊ አመራሮች የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች የተነሱ ሲሆን፣ በማብራሪያውና በቀጣይ የስልጠና አቅጣጫዎች ዙሪያ ሰፊ ውይይት ተካሂዶባቸዋል።

# ርዕሰ -አንቀፅ

## የነገዋ ሀገር እጣ ፈንታ በወላጆች እጅ የተጣለ አደራ!

በአሁኑ ወቅት በማህበረሰባችን ውስጥ እየታየ ያለው የስነ-ምግባር መላላት፣ የመከባበር መጥፋት እና የማህበረሰባዊ እሴቶች መናጋት እያንዳንዱን ዜጋ ሊያሳስብ የሚገባ ትልቅ የደወል ድምጽ ነው:: የሚገርመው ግን፣ ይህንን የስነ-ምግባር ጉድለት ባየን ቁጥር ጣታችንን ወደ ተለያዩ አካላት ለመቀሰር የምናሳየው ፍጥነት ነው:: ለልጆቻችን ስነ-ምግባር መላላት ትምህርት ቤቶችን፣ ሚዲያዎችን፣ ማህበራዊ ትስስር ገጾችን አልፎ ተርፎም "ዘመናዊነትን" ተጠያቂ ማድረግ የተለመደ ሰበባችን ሆኗል:: ሆኖም ግን፣ ትልቁን እውነታ በግልጽ መጋፈጥ ይኖርብናል፤ የስነ-ምግባር ግንባታ መነሻው ደጅ ሳይሆን ቤት ነው!

የአንድ ሀገር ጥንካሬ የሚለካው ከመሰረቱ እንደመሆኑ፣ የማህበረሰብ መሰረቱ ደግሞ ቤተሰብ ነው:: ወላጆች ለልጆቻቸው የመጀመሪያዎቹ እና ዋነኞቹ መምህራን ናቸው:: ዛሬ ላይ በርካታ ወላጆች የኑሮውን ውድነት ለመቋቋም እና ለልጆቻቸው የተሻለ ቁሳዊ ህይወትን ለመፍጠር ሌት ተቀን እንደሚደክሙ ይታወቃል:: ይህ ጥረት የሚደነቅ ቢሆንም፣ ቁሳዊ አቅርቦትን ማሟላት ብቻውን ግን ሙሉ ስብዕና ያለው ዜጋ አይፈጥርም:: ልጆች ከውድ ስጦታዎች በላይ የወላጆቻቸውን ጊዜ፣ ትኩረት፣ ፍቅር እና መመሪያ በጥብቅ ይሻሉ:: በቤት ውስጥ ስርአትን እና የሞራል እሴቶችን ያልቀሰመ ልጅ፣ ነገ ለአደባባይ ሲበቃ ለአካባቢው ብቻ ሳይሆን ለሀገርም ስጋት መሆኑ አይቀሬ ነው:: ወላጆች በንግግራቸው ታማኝነትን፣ በድርጊታቸው መከባበርን፣ በኑሯቸው ደግነትን በተግባር ካላሳዩ በስተቀር በባዶ ምክር ብቻ መልካም ሥነምግባርን መቅረጽ አይቻልም:: የቤት ውስጥ ህጎች ወጥ እና ምክንያታዊ መሆን ይኖርባቸዋል:: ጥፋትን በጥላቻ ሳይሆን በፍቅር ማረም፣ መልካም ባህሪን ደግሞ እውቅና መስጠት የሁሉም ወላጅ የዕለት ተዕለት ተግባር ሊሆን ይገባል:: ትምህርት ቤት የእውቀት መቅሰሚያ፣ ማህበረሰቡ ደግሞ የልምድ መጋሪያ እንጂ የስነ-ምግባር መጀመሪያዎች አይደሉም::

በተለይም በአሁኑ ወቅት የክረምት ወራት በመሆኑና ትምህርት ቤቶች በመዘጋታቸው፣ ልጆች አብዛኛውን ጊዜያቸውን ከወላጆቻቸው ጋር የማሳለፍ ሰፊ ዕድል አላቸው:: ይህ አጋጣሚ ዝም ብሎ የሚታለፍ ረጅም የእረፍት ጊዜ ሳይሆን፣ ወላጆች ልጆቻቸውን በቅርበት እየተከታተሉ፣ በመልካም ስነ-ምግባር እና እሴቶች ኮትኩተው ለመቅረጽ በአንክሮ ሊሰሩበት የሚገባ ወርቃማ ወቅት ነው::

ስለዚህ፣ ነገ የተረጋጋች፣ በስነ-ምግባር የምትከበር እና የሰለጠነች ሀገር እንዲኖረን ከተፈለገ ዛሬ እያንዳንዳችን በዚህ የክረምት እረፍት በቤታችን ላይ በትጋት እንስራ:: ወላጆች ለልጆቻቸው መልካም አርአያ በመሆን ሀላፊነታቸውን በንቃት ሊወጡ ይገባል:: የነገዋ ሀገር የምትገነባው ዛሬ በቤታችን ውስጥ በምናስቀምጠው ጠንካራ የመሰረት ድንጋይ ላይ መሆኑን አንዘንጋ!


ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

### በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለህብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**EARS**

### ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

NCRS

# ቆይታ

## ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እስከ ከፍተኛ ባለስልጣናት የሀብት ምዝገባ ያለው የፖለቲካ ቁርጠኝነት!

የዛሬ ቆይታችን የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የዲጂታል ሀብት ምዝገባ መሪ ስራ አስፈጻሚ ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር ጋር የተደረገ ሲሆን፣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ የሀገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት የሀብት ምዝገባ ማጠናቀቃቸውን ተከትሎ የተመዘገበውን ታሪካዊ ስኬትና የነበረውን የፖለቲካ ቁርጠኝነት በዝርዝር ያብራራል:: መሪ ስራ አስፈጻሚዋ በሂደቱ ውስጥ የወረቀት አሰራርን ወደ ዘመናዊ የዲጂታል ስርዓት (Digital Asset Registration System) ለመቀየር የተከናወኑ ስልታዊ ስራዎችን፣ ያጋጠሙ ቴክኖሎጂያዊና ስነ-ልቦናዊ ተግዳሮቶችን እንዲሁም ከኢንሳ እና ከሌሎች ተቋማት ጋር የተደረጉ የተቀናጁ ድጋፎችን ያነሳሉ:: በተጨማሪም፣ የተመዘገበውን ሀብት ትክክለኛነት እውነታው ጋር ለማመሳከር ከባንኮች፣ ከገቢዎችና ከመሬት አስተዳደር ተቋማት ጋር በቀጣይ የሚዘረጉ የዲጂታል ትስስር ስትራቴጂዎችንና ተጠያቂነትን የማስፈን ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን በስፋት ያመላክታሉ:: መልካም ንባብ!

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-** ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድን ጨምሮ የሀገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት በሙሉ በሚባል ደረጃ የሀብት ምዝገባውን እንዲያጠናቅቁ ተደርጓል:: ይህንን ታሪካዊና አርአያነት ያለው ሀገራዊ ምዝገባ በዚህ ደረጃ ለማስኬድ የተቻለበት ዋናው ሚስጥር ወይም የስኬት ምንጭ ምንድን ነው ይላሉ?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር:-** በጣም ጥሩ እና ወቅታዊ ጥያቄ ነው:: ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ የሀገሪቱ ከፍተኛ አመራሮች በሙሉ በሚባል ደረጃ የሀብት ምዝገባውን ማጠናቀቃቸው፣ በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል ታሪክ ውስጥ ትልቅ ምዕራፍ እና አርአያነት ያለው ተግባር ነው::

ይህንን ታሪካዊ ምዝገባ በዚህ ደረጃ ለማስኬድ እና ለስኬት ለማብቃት ከቻልንባቸው ዋና ዋና ምሰሶዎች፦ 1. ከከፍተኛ አመራሩ የተገኘው የማይናወጥ ቁርጠኝነት፦ የማንኛውም ሀገር የፀረ-ሙስና ትግል ውጤታማ የሚሆነው አመራሩ ራሱ አርአያ ሆኖ ሲገኝ ነው:: ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ከፍተኛ ባለስልጣናቱ ለህጉ መገዛታቸውን በተግባር ማሳየታቸው፣ ለጠቅላላው የመንግስት መዋቅር እና ለህዝቡ ትልቅ መልዕክት አስተላልፏል:: ይህ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ለስራችን ዋናው ግንባር ቀደም ሞተር ሆኖ አገልግሏል:: 2. የህግ የበላይነት እና የህዝብ አደራ ስሜት፦ ሀብትን ማስመዝገብ የሙያ ግዴታ ብቻ ሳይሆን ህገ-መንግስታዊ እና ተቋማዊ ግዴታ ጭምር ነው:: ከፍተኛ ባለስልጣናቱ ህግን የማክበር እና ለህዝብ ግልፅና ተጠያቂ የመሆን አደራቸውን በከፍተኛ ሀላፊነት ስሜት በመወጣታቸው ምዝገባው ያለምንም መስተጓጎል ሊሳካ ችሏል:: 3. የተቀናጀ ክትትል እና የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ትጋት፦ በየደረጃው ያሉ የኮሚሽናችን የስራ መሪዎች



እና ባለሙያዎች፣ የምዝገባ ሂደቱን ደረጃ በደረጃ በመከታተል፣ ቴክኒካዊ ድጋፍ በመስጠት እና ቀጣይነት ያለው ክትትል በማድረግ ባሳዩት ከፍተኛ ትጋት ሂደቱን እጅግ ቀልጣፋ፣ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ እና ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፤ ውጤቱም የቅንጅት ስራችን ማረጋገጫ ነው::

በአጠቃላይ ይህ ስኬት የመንግስት የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ የህግ ተገዢነት እና የኮሚሽናችን ተቋማዊ ብቃትና የቴክኖሎጂ ጥንካሬ በጋራ የተደመሩበት (የመደመራቸው) ውጤት ነው ማለት እችላለሁ::

**ፀረ-ሙስናጋዜጣ ጋዜጣ:-** የእርስዎ መምሪያ (የዲጂታል ሀብት ምዝገባ መሪ ስራአስፈጻሚ) ሂደቱን በቴክኖሎጂና በስትራቴጂ ከመምራት አንጻር የነበረው ሚና ከፍተኛ እንደነበር ይታወቃል:: ለመጣው ውጤት የኮሚሽኑ የላቀ አመራርና የእርስዎ የስራ ክፍል ያበረከቱትን ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ቢያብራሩልን?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር:-** የሀብት ምዝገባውን ካለፉት ዓመታት በተለየ መልኩ ስኬታማ ለማድረግ የእኛ ስራ ክፍል ከኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራር ጋር በመቀናጀት በርካታ ቀጥተኛ አስተዋፅኦዎችን አበርክቷል:: ዋና ዋናዎቹን ስልታዊ እና ቀጥተኛ ሚናዎች በሶስት ከፍለን ማየት እንችላለን፦

1. አሰራሩን ከወረቀት ወደ ዘመናዊ ዲጂታል ስርዓት ማሸጋገር (Digital Transformation)፦ ቀደም ሲል የነበረው የወረቀት አሰራር ጊዜ የሚወስድ እና በርካታ ተግዳሮቶች የነበሩበት ነበር:: ኮሚሽኑ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የዲጂታል ኢትዮጵያ የሀብት ምዝገባ ስርዓትን (Ethiopian Asset Registration System-EARS) በላቀ የቴክኖሎጂ ደረጃ በማልማት፣ በማዘመን እና ደህንነቱ አስተማማኝ እንዲሆን በማድረግ ስራ ላይ አውሏል:: ይህ ስርዓት ሀብት አስመዝጋቢዎች ባሉበት ሆነው በምስጢራዊነት እና በጥንቃቄ መረጃቸውን እንዲያስገቡ ያስቻለ ዋነኛ የቴክኖሎጂ መሰረት ነው:: ስራ ክፍላችንም ይህን ተግባር በየዕለቱ በመከታተል የተጠናከረ የድጋፍ ስራዎች እየሰራ ይገኛል:: 2. ስልታዊና ተለዋዋጭ የክትትል ስልቶችን መቅረፅ፦ ቴክኖሎጂው መኖሩ ብቻውን በቂ አይደለም፤ ምዝገባውን የሚመራበት ስልት ያስፈልጋል:: ስራ ክፍሉ ምዝገባውን ከመደበኛ የስራ ሂደት በተለየ መልኩ በልዩ ስትራቴጂ መርቷል:: በየዘርፉና ተቋማቱ በመከፋፈል የተለየ የቴክኒክ ድጋፍ ቡድን መድበናል፣ ምዝገባውን ያጠናቀቁ እና ያላጠናቀቁትን በመለየት፤ የክትትል ዝርዝር በማዘጋጀት ክፍተቶችን በየቀኑ ስንገመግም ቆይተናል:: ይህ ስልታዊ ክትትል ምዝገባው በተሻለ ሁኔታ ተፈጻሚ እንዲሆን አድርጓል:: 3. የኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራር የሰጠው ያልተቆጠበ ድጋፍ፦ ይህ ሁሉ የቴክኖሎጂ እና የስልት ዝግጅት ውጤታማ ሊሆን የቻለው የኮሚሽናችን ከፍተኛ አመራሮች ለስራው የሚያደርጉት ክትትል፣ ፈጣን ውሳኔዎች እና ያልተቆጠበ ተቋማዊ ድጋፍ ነው:: አመራሩ ለዲጂታል ስርዓቱ መዘርጋት አስፈላጊውን እገዛ በማድረግ በየደረጃው ያሉ ማነቆዎችን ፈጣን ውሳኔ በመስጠት በመፍታቱ የእኛ ስራ ክፍል ስራውን በተሻለ ፍጥነት እንዲያከናውን ትልቅ አቅም ሆኖናል::

በመሆኑም የስራ ክፍሉ ለተቋማት የላቀ የቴክኖሎጂ አፈጻጸም ላይ ያደረገው ድጋፍ እና ስልታዊ ክትትል፣ በሲስተሙ የተሻለ ለመስራት የኢንሳ ያልተቋረጠ እገዛ ጋር ተዳምሮ ነው ዛሬ የምናየውን የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ያስቻለው::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ:-** ይህ ምዝገባ በየመንግስት ተቋማቱ ባሉ የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችና አመራሮች እገዛ ጭምር የተከናወነ ነው:: የእነዚህ ክፍሎች ቁርጠኝነትና አበርክቶ በስራችሁ ላይ የፈጠረው ተጽዕኖ ምን ይመስል ነበር?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር:-** የእነሱ ቁርጠኝነትና አበርክቶ በስራችን ላይ የፈጠረው ተጽዕኖ እጅግ ከፍተኛ እና አዎንታዊ የነበረ ሲሆን፣ በዋናነት በሚከተሉት ነጥቦች ሊጠቃለል ይችላል፦የመረጃ ተደራሽነትን ማፍጠን፦ በየተቋማቱ ያሉ የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች እያንዳንዱ የስራ ሀላፊ እና ሰራተኛ ስለ ዲጂታል ምዝገባው በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው በማድረግ፣ የምዝገባ ጥሪዎችን በፍጥነት በማድረስና በማስተባበር ረገድ እንደ ዋና ድልድይ ሆነው አገልግለዋል:: የቅርብ ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት፦ ኮሚሽኑ

የዘረጋውን የዲጂታል የሀብት ምዝገባ ስርዓት ተመዝጋቢዎች በየተቋማቸው ሆነው በቀላሉ እንዲጠቀሙበት የፊት-ለፊት ድጋፍ በመስጠት እና የተጠቃሚ ስምና የይለፍ ቃል (Password) ማስተካከልን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ከእኛ ጋር በመቀናጀት ሂደቱን እጅግ አቅልለውታል። ባለቤትነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፦ የየተቋማቱ የበላይ አመራሮች ምዝገባውን የራሳቸው ተቋማዊ ግዴታ አድርገው በመውሰድና በቅርብ በመከታተል፣

ለስራው እገዛ እንዲያደርጉ እና በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መረጃቸውን እንዲያጠናቅቁ አስቻይ ሁኔታ እንዲፈጠር ትልቅ ተፅዕኖ ፈጥረዋል።

ባጭሩ በየተቋማቱ ያሉ የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች እና አመራሮች ያሳዩት የተቀናጀ አጋርነት እና ስልታዊ ክትትል በተሻለ ውጤት ለማጠናቀቅ እጅግ ወሳኝ የሆነ ተቋማዊ ጉልበት ሆኖናል ማለት እችላለሁ።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** የሀብት ምዝገባን ከባህላዊ አሰራር ወደ ዲጂታል ስርዓት መቀየር ቀላል እንዳልሆነ ይታመናል። በሂደቱ ላይ ያጋጠሙ ዋና ዋና ተቋማዊ፣ ቴክኖሎጅያዊና የስነ-ልቦና መሰናክሎች ምን ነበሩ? የእርስዎ ክፍል እነዚህን ተግዳሮቶች እንዴት አለፋቸው?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፡-** ማንኛውንም ሀገራዊ አሰራር ከወረቀት/ከማኑዋል ወደ ዲጂታል መቀየር ቴክኖሎጂን ከመዘርጋት ባለፈ በርካታ ውስብስብ ችግሮችን ማለፍን ይጠይቃል። በዚህ ሂደት ውስጥ ያጋጠሙን ተግዳሮቶች፦የስነ-ልቦና ተግዳሮት፦ ሰዎች ለዓመታት ከለመዱት የወረቀት አሰራር ወጥተው አዲስ ቴክኖሎጂ ሲያጋጥማቸው "ሲስተሙ መረጃዬን ይይዝልኛል? ሚስጥሬ ይጠበቃል?' የሚል የስጋት እና የጥርጣሬ ስሜት መፈጠሩ ተፈጥሯዊ ነበር። ይህ አዲሱን የዲጂታል አሰራር የመቀበል የስነ-ልቦና ተግዳሮት ነበር። ቴክኖሎጂያዊ መሰናክል፦ አንዳንድ ቦታዎች የሚታዩ የኢንተርኔት መቆራረጦች፣ የተመዝጋቢዎችና የአስተባባሪዎች የዲጂታል ክህሎት ውስንነቶች እና እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የመረጃ ፍሰት በአንድ ጊዜ ሲስተሙ ላይ በሚያርፍበት ወቅት በሲስተሙ የሚፈጠሩ የቴክኒክ ጫናዎች ነበሩ።

ለእነዚህ ተግዳሮቶች መፍትሄ ለመስጠት የዲጂታል ስርዓቱ የሳይበር ደህንነቱ (Cybersecurity) እጅግ የላቀ መሆኑን እና መረጃዎችን በከፍተኛ ምስጢራዊነት እንደሚይዝ ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ ፈጠርን። በቀላሉ የሚረዱ የቪዲዮ እና የፅሁፍ መመሪያዎችን (User Manuals) በማዘጋጀት ስጋታቸውን ወደ መተማመን ቀየርን። የኢንተርኔት ፍጥነትን ታሳቢ ያደረገ ቀላል እና ቀልጣፋ ሲስተም ሆኖ እንዲያገለግል በማሻሻል ከኢንሳ ጋር በመተባበር አበለፀግን። በተጨማሪም የእኛ መምሪያ የቴክኒክ ባለሙያዎች የይለፍ ቃል መልሶ ማስተካከልን ጨምሮ ማንኛውንም የቴክኒክ ችግር በስልክ እና በአካል ምላሽ የሚሰጥ የድጋፍ ቡድን በየዘርፎችና ተቋማት ከፋፍሎ በማደራጀት ምዝገባው እንዳይስተጓጎል አድርገናል። በየተቋማቱ ያሉ የምዝገባ ሁኔታዎችን በየቀኑ በዲጂታል ዳሽቦርድ (Dashboard) በመከታተል፣ ያላጠናቀቁትን በቅርብ የመከታተያ ዝርዝር እየለየን ፈጣን ምላሽ እንዲሰጡ አድርገናል። በአጠቃላይ ልማዳዊ የወረቀት አሰራርን የመቀየር ጉዞው ከባድ የነበረ ቢሆንም፣ የስራ ክፍላችን ባለሙያዎች ያሳዩት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል ስራ እና የኮሚሽኑ አመራሮች ለስራው የሰጡት ትኩረት ተግዳሮቶቹን እንድንወጣና ይህንን የተሻለ ውጤት እንድናስመዘግብ አስችሎናል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** የሀብት ምዝገባ በራሱ የመጨረሻ ግብ ሳይሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ ነው። አሁን ላይ ትኩረት የሚሻው ጉዳይ የተመዘገበው ሀብት ትክክለኛነት ጉዳይ ነው። የእርስዎ መምሪያ የተመዘገበውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እና መሬት ላይ ካለው ሀብት ጋር ለማመሳከር ለወደፊቱ ምን አይነት የቴክኖሎጂና የስራ ስትራቴጂ ነድፏል?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፡-** የሀብት ምዝገባ በራሱ የመጨረሻ ግብ ሳይሆን፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን የምንጠቀምበት የመጀመሪያው ምዕራፍ የሙስና መከላከያ መንገድ ነው። በሀብት ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 668/2002 መሰረት የተመዘገበን ሀብት ትክክለኛነት የማጣራት ስራ የሚሰራው ኮሚሽኑ ሲጠረጥር ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ወይም እንዲጣራ ከሚመለከተው ተቋም ትዕዛዝ ሲሰጥ ነው። የሀብት ምዝገባውን ወደ ዲጂታል በመቀየር የተሻለ አፈጻጸም ማስመዝገብ እንደተቻለው ሁሉ የሀብት ምዝገባ መረጃዎችን ትክክለኛነት በማረጋገጥ እና በመፈተሽ ችግር ባለባቸው ላይ የተጠያቂነት አሰራርን ለማሳደግ አጠናክረን የምንሰራ ይሆናል።

ለዚህም፦ ከመረጃ ሰጪ ተቋማት ጋር የዲጂታል ትስስር መፍጠር፦ የተመዘገበውን መረጃ ትክክለኛነት በሰው ኃይል ብቻ ማረጋገጥ ሰፊ ጊዜና ጉልበት ይጠይቃል። ይህን አሰራር በማሻሻል ተግባራዊ ለማድረግ መረጃ ከሚሰጡ ሌሎች የመንግስት እና የግል ተቋማት ጋር የዲጂታል ትስስርን በመፍጠር መረጃዎችን በተቀላጠፈና ሚስጥራዊነቱን በጠበቀ ሁኔታ መረጃ ለመቀባበልና ለመስራት አቅደናል ። ለምሳሌ፦ ከባንኮች፣ ከገቢዎች ሚኒስቴር (የግብር መረጃ)፣ ከይዞታ ማረጋገጫ እና መሬት አስተዳደር (የቤትና መሬት መረጃ) እንዲሁም ከትራንስፖርት ሚኒስቴር (የተሽከርካሪ መረጃ) ጋር የቴክኖሎጂ ትስስር በመፍጠር፣ የተመዘገበው መረጃ እና በተቋማቱ ያሉ ተጨባጭ መረጃዎች አውቶማቲክ በሆነ መንገድ እንዲጣቀሱ እና እንዲረጋገጡ ይደረጋል።

በስጋት ግምገማ ላይ የተመሰረተ የሀብት ምዝገባ ትክክለኛነት ማጥራት፦ በአዋጁ መሰረት ሁሉንም ተመዝጋቢ በአንድ ጊዜ በእኩል ደረጃ ማጥራት ሳይሆን የተጋላጭነትና የስጋት ደረጃን መሰረት ያደረገ አሰራር እንከተላለን። ከፍተኛ የሙስና ስጋት ያለባቸውን የስራ መደቦች፣ በምዝገባ ወቅት አጠራጣሪ ወይም ያልተመጣጠኑ የሀብት ፍሰቶች የታዩባቸውን የምዝገባ መረጃዎችን ቅድሚያ በመስጠት ካለው መረጃ ጋር የማመሳከር እና የማረጋገጥ ስራውን በልዩ ትኩረት እናከናውናለን። የህዝብ ተሳትፎ እና የጥቆማ ስርዓትን ማጠናከር፦ መሬት ላይ ያለውን እውነታ ለማወቅ የህዝብ ተሳትፎ ወሳኝ ነው። ህብረተሰቡ ወይም ጥቆማ አቅራቢዎች በህገ-ወጥ መንገድ ሀብት የሚያከማቹ ግለሰቦች ላይ የሚያቀርቧቸውን የሀብት መረጃ ጥቆማዎች ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ የዲጂታል ጥቆማ መቀበያ ስርዓት(በኮሚሽኑ ስር ያለው ብሄራዊ የሙስና ጥቆማ ስርዓት-NCRS) ተደራጅቷል። ይህ ደግሞ የሀብት ምዝገባ ትክክለኛነት ማረጋገጫ ዋና አጋዥ ያደርገዋል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** የዲጂታል ስርዓቱን ከተለያዩ መረጃ-አቅራቢ ተቋማት (ለምሳሌ፡ ከባንኮች፣ ከገቢዎች፣ ከቤትና መሬት ምዝገባ ወዘተ) ጋር በቀጥታ የማገናኘት ስራ አፈጻጸም አሁን ላይ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ለወደፊቱስ ምን ይታሰባል?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፡-** በህጉ መሰረት የሀብት ምዝገባ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከመረጃ ሰጪ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየተሰራ ይገኛል። ተቋማቱ ኮሚሽኑ የሚጠይቃቸውን መረጃዎች አረጋግጠው ይልካሉ፡ ፡ ይህንንም ተግባር ቀደም ሲል በወረቀት መረጃ መቀባበል ይሰራ የነበረውን የግለሰቦችን የሀብት ምስጢር ለመጠበቅና የመረጃ ብክነት እንዳይኖር አሁን ላይ መረጃውን በኢ-ሜል ብቻ የምንቀባበል ሲሆን በቀጣይ አሰራሩን ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል በመቀየር የሚሰራ ይሆናል። የወደፊት እቅዳችንም ይህንን ትስስር ወደ ክልሎችም በማካተት ሙሉ ሀገራዊ ዲጂታል አተገባበር በመቀየር፣ ኢትዮጵያ በዲጂታል ዘመን የምትመራው ዘመናዊ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት የፀረ-ሙስና ስርዓት ባለቤት እንድትሆን ማድረግ ነው።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** ተጨማሪ ማብራሪያ ካለዎት?

**ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር፡-** በጣም አመሰግናለሁ! እንደ ማጠቃለያ እና ተጨማሪ ማብራሪያ ዋና ዋና ነጥቦችን ማስመር እፈልጋለሁ፦

በመጀመሪያ ይህ ስኬት የጠቅላይ ሚኒስቴሩ አመራር ቁርጠኝነት ውጤት መሆኑ ነው፦ የአርአያነት መልዕክት ነው። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አህመድን ጨምሮ የከፍተኛ አመራሮቻችን ለህግ መገዛት እና ሀብታቸውን በግልጽ ማስመዝገባቸው፣ ወደ ታች ባለው የመንግስት መዋቅር ውስጥ ለሚገኙ መካከለኛ የስራ መሪዎችና ባለሙያዎች እጅግ ጠንካራ የሆነ የአርአያነት መልዕክት ያስተላልፋል። "ህግ ከሁሉም በላይ ነው' የሚለውን መርህ በተግባር ያረጋገጠ ተግባር ነው። ሌላው የሀብት ምዝገባውን ከልማዳዊና ወረቀት አሰራር ወደ ዲጂታል ማሸጋገራችን እና የተቋማት ከፍተኛ አመራሮች በሙሉ በሚባል ደረጃ እንዲመዘገቡ መደረጉ የሚያሳየው ኮሚሽናችን የጀመረው ተቋማዊ የሪፎርም እና የዘመናዊነት ጉዞ ፍሬ እያፈራ መሆኑን ነው። ቴክኖሎጂን ታጥቆ መስራት ስራን እንዴት እንደሚያቀልጥፍ በተግባር ያየንበት ታሪካዊ ምዕራፍ ነው። በመጨረሻም ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚኖር ትስስር፦ ኮሚሽናችን የጀመረውን የዲጂታል አሰራር ይበልጥ በማጠናከር፣ በቀጣዩ ምዕራፍ ከተለያዩ መረጃ-አቅራቢ ተቋማት ጋር የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር በማስፋት፣ ትኩረት በሚፈልጉ የስራ ዘርፎች እና አጠራጣሪ ምዝገባዎች ላይ የተመዘገበው ሀብት ትክክለኛነት እንዲረጋገጥ እናደርጋለን። ዜጎችም በዚህ የፀረ-ሙስና እና የባለቤትነት ጉዞ ውስጥ እንደሁልጊዜው ከኮሚሽናችን ጎን በመቆም እና ጥቆማዎችን በመስጠት አጋርነታቸውን እንዲያጠናክሩ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

እናመሰግናለን!

# ሳይቃጠል በቅጠል

## በዓመት 88 ሚሊዮን ብር ለዳቦ

### የደብረታቦር ዩኒቨርሲቲን በጀት የበላው ረዥም ውል እና ከጀርባው ያለው አከራካሪ ግዥ

ባለፉት አስርት ዓመታት በደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ አንድ አስገራሚ ታሪክ ሲደገም ቆይቷል። ዩኒቨርሲቲው የራሱ የዳቦ መጋገሪያ ማሽን ባለመኖሩ ብቻ፣ በየዓመቱ ከአንድ የግል አቅራቢ ጋር ውል እያደሰ ለተማሪዎች ዳቦ ለማቅረብ በሚሊዮኖች የሚቆጠር የመንግስት በጀት ይፈስ ነበር።
ነገር ግን በፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ብሔራዊ የሙስና መቀበያ ስርዓት (NCRS) በኩል የደረሰ ጥቆማ፣ ይህንን ለዓመታት የዘለቀ አሰራር እና ዩኒቨርሲቲው ችግሩን ለመቅረፍ የሄደበትን አከራካሪ የኮንትራት መንገድ ይፋ አድርጓል። የኮሚሽኑ አስቸኳይ ሙስና መከላከል ቡድን ባደረገው ሰነድ-ተኮር ማጣራት የደረሰበትን እውነታ ይፋ አድርጓል።

ማጣራቱ መጋረጃውን የገለጠው በዩኒቨርሲቲው እና “እያሱ መንገሻ” በተባለ የዳቦ አቅራቢ ድርጅት መካከል በነበረው የዋጋ ልዩነት ላይ ነው። የገበያ እውነታው፦ በአሁኑ ወቅት በደብረታቦር ከተማ አንድ ባለ 150 ግራም ዳቦ በ12.00 ብር እየተሸጠ ይገኛል። የዩኒቨርሲቲው ውል፦ ዩኒቨርሲቲው ግን ከአቅራቢው ድርጅት ያንኑ ተመሳሳይ ዳቦ በ21.92 ብር (ከገበያ ዋጋው በ9.92 ብር በበለጠ) ሲረከብ ቆይቷል። አጠቃላይ ወጪው፦ ዩኒቨርሲቲው ለዚህ አቅርቦት ብቻ በዓመት እስከ 88,358,400.00 ብር የሚደርስ እጅግ የተጋነነ የመንግስት በጀት ሲከፍል እንደነበር ተደርሶበታል። ይህንን ከፍተኛ ወጪ ለማስቆም ዩኒቨርሲቲው ከ2014 እስከ 2017 ዓ/ም በተደጋጋሚ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የራሱን የዳቦ ማሽን ለመግዛት ግልፅ ጨረታ ቢያወጣም፣ አንድም ተጫራች ሊቀርብ አልቻለም።
ግልፅ ጨረታው በተደጋጋሚ ሳይሳካ ሲቀር፣ ዩኒቨርሲቲው ግዥውን በውስን ጨረታ (Restricted Bidding) ለመፈጸም ወሰነ። የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣንም በአዋጅ ቁጥር 1333/2016 መሠረት ግዥው



በልዩ ሁኔታ በውስን ጨረታ እንዲፈጸም ፈቀደ። ነገር ግን እዚህ ጋ አዲስ አከራካሪ ነጥብ ተነሳ፡- የፌደራል የመንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1073/2017 ለውስን ጨረታ የእቃ ግዥ የገንዘብ ጣሪያ 12 ሚሊዮን ብር ብቻ አድርጎ ቢደነግግም፣ የዩኒቨርሲቲው አሸናፊ የጨረታ ዋጋ ግን 17,581,000.00 ብር (ከጣሪያው በ5.5 ሚሊዮን ብር በበለጠ) ሆኖ ጸድቋል።
የግዥ ባለስልጣኑ “ጨረታ አንዴ ከወጣ የዋጋ ጣሪያው አይገድብም” የሚል ምላሽ የሰጠ ቢሆንም፣ የኮሚሽኑ አስቸኳይ ሙስና መከላከል ቡድኑ ግን ይህ አሰራር በጥብቅ የግዥ ዲሲፕሊን መመራት እንደነበረበት ይጠቁማል።
ሌላው በማጣራቱ የተገኘው ትልቅ ግኝት የጨረታ ኮሚቴው የቴክኒክ ግምገማ አፈጻጸም ነው። በህጉ መሠረት 70% ለቴክኒክ እና 30% ለፋይናንሻል (ዋጋ) ግምገማ መመደብ ነበረበት። ሆኖም ተጫራቾቹ ከዩኒቨርሲቲው የገዙትን ሰነድ ቀጥታ ሞልተው እና ማህተም አድርገው ስላስገቡ ብቻ የቴክኒክ መስፈርቱን እንዳሟሉ ተቆጥረዋል። ኮሚቴው የቴክኒክ ውጤት ደረጃን ሳይገልጽ በቀጥታ ወደ ዋጋ ውድድር አሳልፏቸዋል። ከተጋበዙት 8 ተጫራቾች መካከል ህጋዊ ፈቃድ የሌላት አንዷ ስትሰረዝ፣ ቀሪዎቹ 7 ተወዳዳሪዎች ያቀረቡት የዋጋ ዝርዝር የሚከተለውን ይመስል ነበር፡ - ጌታሰው ተገኝ 17,581,000.00 1ኛ (አሸናፊ)፣ኤል ጠቅላላ የንግድ ስራዎች 18,577,000.00 2ኛ፣ መንገሻ ማለደ 18,899,900.00 3ኛ፣ብርሀኑ አሳዬ 20,287,000.00 4ኛ፣ ገነት ሽፈራ 21,436,000.00 5ኛ፣ ማዚብ እንጂነሪንግ 22,219,698.30 6ኛ እና ገብሬ ሞላ 28,931,943.00 7ኛ በመሆን ለጨረታ ቀርበው ነበር።
የጥናት ቡድኑ ምንም እንኳን በሂደቱ ላይ የህግና የአሰራር ክፍተቶች ቢታዩም፣ አንድ ትልቅ እውነታን ግን ሳይመሰክር አላለፈም፦ ይህ ግዥ መፈጸሙ ለመንግስት ትልቅ እፎይታ ነው። ዩኒቨርሲቲው በየዓመቱ ለዳቦ ግዥ ከሚያወጣው 88.3 ሚሊዮን ብር አንጻር፣ በ17.5 ሚሊዮን ብር የአንድ ጊዜ ወጪ የራሱን ማሽን መግዛቱና መትከሉ ዘላቂ መፍትሄ ከመሆኑም በላይ የተጋነነ ወጪን ሙሉ በሙሉ የሚያስቀር ነው። በአሁኑ ወቅት የማሽኑ ግዥ ተፈጽሞ የተከላ ስራው መጠናቀቁም ታውቋል።
የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች፡- የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1073/2017 ለውስን ጨረታ የእቃ ግዥ የተቀመጠው 12 ሚሊዮን ሆኖ እያለ ተጫራቹ በ17,581,000.00 ብር አሸናፊ መሆኑ፣ የተጫራቾችን የቴክኒክ ምዘና ለመገምገም የተቀመጠ መለኪያ ነጥብ በአግባቡ ሳይገመገም ተጫራቾች ከዩኒቨርሲቲው የገዙትን ሰነድ በቀጥታ ሞልተው እና ማህተም አድርገው ያስገቡትን ሰነድ እንደ ተሟላ በመቁጠር ብቻ ገምጋሚ ኮሚቴ ያወዳደረ መሆኑ፣ በመመሪያ ቁጥር 1073/2017 አንቀፅ 61 ንዑስ አንቀፅ 16 “ሀ “ መሰረት 70% ለቴክኒካል ግምገማ እና 30% ለፋይናንሻል ግምገማ ሆኖ እያለ በዚህ ጨረታ ላይ ግን ሁሉም ተጫራጮች የቴክኒካል መስፈርቱን በተሸጠላቸው ሰነድ ቀጥታ ኮፒ ስላደረጉ ብቻ የቴክኒክ መሰፈርት እንዳሟሉ በመቁጠር ተጫራቾችን በፋይናንሻል ግምገማ ብቻ ያወዳደሩ መሆኑን፣ ዩኒቨርስቲው ባለ 150 ግራም ዳቦ ከተማው ላይ በ12 ብር እየተሸጠ ባለበት ወቅት ከአቅራቢው 21.92 ብር ለአስር ዓመት ሲረከብ የቆዩ መሆኑ፣ ስለሆነም ከላይ የተመለከቱትን መሰረታዊ ኃሳቦች በመመልከት የሚከተለው ምክረ ኃሳብ ቀርቧል።
የውሳኔ ምክረ -ሀሳብ ፡- በአጠቃላይ የጥናት ቡድኑ ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በክፍተት የተመለከተ ሲሆን እና የዳቦ መጋገሪያ ማሽኑም ግዥ ተፈፅሞ የተከላ ስራ ላይ እንደሚገኝ ከተላከው የፎቶ ማስረጃ እንዲሁም ዩኒቨርሲቲዉ በዓመት ለዳቦ ግዥ ከሚያወጣዉ 88,358,400.00 ብር ወጭ አኳያ የዳቦ ማሽን ግዥ አሰፈላጊና የመንግስትን በጀት አለአግባብ ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግና መቆም ያለበት ጉዳይ መሆኑ ይታመናል። ነገር ግን የማሽኑ ግዥ በግዥ አዋጅ የተቀመጠውን የገንዘብ ጣሪያ ያለፈና የግዥ ባለስልጣኑ የጻፈው ደብዳቤ የግዥ ህጉን ተከትላችሁ ስሩ ከማለት በስተቀር ግዥዉ እንዲካሄድ የፈቀደበት ሆኖ አይታይም።ይሁን እንጅ ግዥ ባለስልጣን አንዴ ጨረታ ከወጣ የዋጋ ጣሪያ የማይገድብ መሆኑን ገልጿል። በመሆኑም ዩኒቨርሲው ግዥዉን ለመፈፀም የመንግስትን ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና መመሪያ በጥብቅ ዲሲፕሊን በመከተል እና የግልጽነትና የተጠያቂነትን አሰራርን ባከበረ መልኩ ተግባራዊ በማድረግ ለኮሚሽኑ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማለት ምክረ-ሀሳብ አቅርቧል።

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

## የሞተን ሠራተኛ ስም በመጠቀም በሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል የፈጸመች ተከሳሽ በፅኑ እስራትና በገንዘብ ተቀጣች

የሞተን ሠራተኛ ስም በመጠቀም መንግስታዊ ሰነዶችን ወደ ሀሰት በመለወጥና በሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል የፈጸመች ተከሳሽ በፅኑ እስራትና በገንዘብ መቀጣቷን የደቡብ ወሎ ዞን ፍትህ መምሪያ አስታወቀ።

በደቡብ ወሎ ዞን ፍትህ መምሪያ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች የሥራ ሂደት አስተባባሪ ዐቃቤ ህግ ምናለ ደርሶልኝ የፍርድ ሂደቱን በተመለከተ ለአሚኮ እንደገለፁት፣ የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ነዋሪዋ ተከሳሽ ወ/ሮ ሉባባ መሀመድ ይማም፣ በሀሰት የተዘጋጀ የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ኮሚቴ ውሳኔ፣ በኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ከተማና መሰረተ ልማት መምሪያ ለ99 ዓመት የተሰጠ ነው የሚል ሀሰተኛ የሊዝ ውል እና ጥቅምት 2 ቀን 2010 ዓ.ም የተዘጋጀ የካርታ ቁጥሩ 13812 የሆነ ሀሰተኛ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት 150 ካ.ሜ የቀጠና ዋጋው 487,500 ብር የሆነ የከተማ ቦታ በስሟ በማሰራትና በመያዝ ማንነታቸው ተለይቶ ካልታወቁ የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ከተማና መሰረተ ልማት መምሪያ ሠራተኞች ጋር በመመሳጠርና የጥቅም ትስስር በመፍጠር በ2012 ዓ.ም የሞተን ሠራተኛ ስም በመጠቀም በተከሳሽ ስም የተዘጋጁ ሀሰተኛ ሰነዶችን በከተማ አስተዳደሩ ከተማና መሰረተ ልማት መምሪያ መዝገብ ቤት ውስጥ የባለቤትነት ማህደር እንዲዘጋጅላትና ወደ መዝገብ ቤት እንዲገባ በማድረግ እየተገለገለች እንደነበር አንስተዋል።

ድርጊቱ በሙስና ወንጀል ምርመራ ተጣርቶ በ1ኛ ክስ መንግሥታዊ ሰነዶችን ወደ ሀሰት መለወጥና በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል የሙስና ወንጀል እና በ2ኛው ክስ በሀሰተኛ ሰነድ የያዘችው 150 ካሬ ሜትር ቦታ እንዲወረስ ክስ ቀርቦባት በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለዘጠኝ ወር ያህል ክርክር ሲደረግበት መቆየቱን ነው አቶ ምናለ የተናገሩት።


የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባስቻው ችሎት ተከሳሽ በ2 ዓመት እስራትና በ2 ሺህ ብር መቀጮ እንድትቀጣና በስሟ በሀሰት ያሰራችው ካርታ ተሰርዞ በዚህ ካርታ የተያዘው ግምቱ 487,500 ብር የሆነ 150 ካ.ሜትር የህዝብና የመንግስት ቦታ ወደ ኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር መሬት መምሪያ የመሬት ባንክ ገቢ እንዲደረግ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን አብራርተዋል።

የቅጣት ውሳኔው ማንኛውም ሰው ከወንጀል ድርጊት ተጠቃሚ መሆን እንደማይችልና በሙስና የተገኘን ሀብት አሁን በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተተገበረ ካለው የህግ ማዕቀፍ አንጻር ፈጽሞ መጠቀም እንደማይቻል የገለፁት አቶ ምናለ፣ በማንኛውም ሁኔታም ወደ ህጋዊነት መቀየር እንደማይችል የሚያስገነዝብ ውሳኔ ነው ብለዋል።

መሰል የወንጀል ድርጊት የሚፈፅሙ ግለሰቦች ከወንጀል ተጠያቂነት ውጪ ሊያተርፉት የሚችሉት ጥቅም እንደማይኖር በመረዳት ተመሳሳይ የወንጀል ተግባር ከመፈፀም ሊታቀቡ ይገባል ብለዋል።

# መልካም ዜጋ

## አርቲስት ለማ ጉያ የሙስና ቀንደኛ ጠላት እና የእውነት ምስክር



እውነተኛ መልካም ዜግነት የሚለካው በትናንሽ የግል ጥቅሞች ላይ ሳይሆን፣ ለአገርና ለወገን በሚበረከት የላቀ አስተዋፅኦ፣ ስለ እውነት ለመቆም በሚደረግ ተጋድሎና ለጋራ እድገት በሚታይ ታማኝነት ነው። መልካም ዜጋ ማለት የማህበረሰቡን ህመም የራሱ አድርጎ የሚሰማው፣ ብልሹ አሰራርና ሙስና አገርን ሲያደቅቁ ዝም ብሎ የማይመለከት፣ ይልቁንም በተሰማራበት የሙያ መስክ ሁሉ እውነትንና ፍትህን አንግቦ የለውጥ ብርሃን ለመሆን የሚተጋ ህያው የሀገር ባለውለታ ነው። ለአገርና ለወገን በሚፈስ እውቀት፣ በሚሰጥ ፍቅርና ስለ እውነት ለመቆም በሚደረግ ተጋድሎ ነው። በዚህ ሚዛን ሲለካ ደግሞ ክቡር አርቲስት ለማ ጉያ በግንባር ቀደምትነት የሚሰለፉ ድንቅ የጥበብ ሰውና የሀገር ባለውለታ ናቸው። ለማ ጉያ የስዕል ብሩሻቸውን ቀለም ለመቀቢያ ብቻ ሳይሆን፤ የማህበረሰቡን ብሶት፣ እውነትና ፍትህ ለመቅሰሚያነት የተጠቀሙበት የታላቅነት ማረጋገጫቸው ነው።

ሙስና የሀገርን እድገት የሚበላ፣ ማህበራዊ ፍትህን የሚያናጋና የድሆችን ጉሮሮ የሚዘጋ ደዌ መሆኑን ቀድመው የተረዱት አርቲስቱ፣ ይህንን እኩይ ተግባር በስዕሎቻቸው በዝርዝር አጋልጠዋል። በተለይም ስልጣንን ለግል ጥቅም ማዋልን፣ የህዝብን ሀብት መዝረፍንና የሀገርን ንብረት ማባከንን ረቂቅና ልብ በሚነካ የጥበብ ስራዎቻቸው በግልፅ ተዋግተዋል። በዚህም ጥበብ ለመዝናኛ ብቻ ሳይሆን፣ ለማህበረሰብ ለውጥና ለፀረ-ሙስና ትግል ታላቅ መሳሪያ መሆን እንደምትችል በተግባር አሳይተዋል። ከአሁን በፊት በኪነ-ጥበብ አምዳችን ላይ ያስነበብናችሁና ሙስናን በብሩሽ የተዋጉበት "ቋንጣ" የተሰኘው ድንቅ የስዕል ስራቸው የዚህ እውነት ህያው ምስክር ነው። በመሆኑም ይህንን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ብልሹ አሰራር በስዕሎቻቸው የታገሉ ጀግና በመሆናቸው፣ ዛሬ በ"መልካም ዜጋ' አምዳችን ልናወሳቸው ወደድን።

ለማ ጉያን "መልካም ዜጋ' የሚያሰኛቸው ምንድን ነው?

ስለ እውነት መቆም፦ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በስዕል ማጋለጥ ትልቅ ድፍረትንና የላቀ የሀገር ፍቅርን ይጠይቃል። አርቲስት ለማ ጉያ ስልጣንና ጉልበት ያላቸውን አካላት ሳይፈሩ፣ በስራዎቻቸው አማካኝነት የህዝብ አይንና ጆሮ በመሆን በታማኝነት አገልግለዋል። ጥበብን ለህዝብ ጥቅም ማዋል፦ የሰውን ልጅ ህሊና ሊያነቃቁ፣ ህዝብ መብቱንና ግዴታውን እንዲያውቅ ሊያደርጉ የሚችሉ በርካታ አስተማሪ ስዕሎችን በተለየ ጥበባቸው በቆዳ ላይ በመሳል ለታሪክ አስቀምጠዋል። አርአያነት፦ በትውልድ ላይ በጎ ተፅዕኖ ማሳረፍ የመልካም ዜግነት ቁንጮ መገለጫ ነው። ለማ ጉያ በሰሩት ስራ ሁሉ ለቀጣዩ ትውልድ የሞራል ልዕልናን፣ ታማኝነትንና የሀገር ፍቅርን በተግባር አስተምረው አልፈዋል።

አርቲስት ለማ ጉያ በኢትዮጵያ ባህልና ጥበብ ላይ ካሳረፉት ታላቅ አሻራ ባሻገር፣ ለሀገራቸው ሰላም፣ እድገትና ፍትሃዊነት በስራዎቻቸው የሞገቱ እውነተኛ የሀገር ጠበቃ ነበሩ። ሙስናን በብሩሻቸውና በቆዳ ላይ በከተቧቸው ህያው ምስሎች የተዋጉበት መንገድ ዘላለማዊ ክብርን ያሰጣቸዋል፤ በትውልድ ዘንድም ሁሌም የ"መልካም ዜጋ' ተምሳሌት አድርጓቸዋል። እሳቸው የለኮሱት የእውነትና የጥበብ ብርሃን ሙስናንና ጨለማን በመዋጋት ረገድ ለዘላለም ሲያበራ ይኖራል። እናም ማንኛውም ዜጋ በተሰማራበት ሁሉ ለሰዎች ብርሀን፣ ለትውልድ አርዓያ ተግባር በመፈጸም መልካም ዜግነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል የሚል የዝግጅት ክፍሉ መልክት ያስተላልፋል።

# ኪነ-ጥበብ

## የሀገር ጠንቅ

ስግብግብነት ነግሦ በራስ-ወዳድነት፣
ሁሉን ለኔ ማለት በስልጣን መመካት።
የበላዮችን መጥለፍ ለአንዱ ማቀባበል፣
መብትን ለማስከበር በጉቦ መደለል።
ማጭበርበር ሌብነት ሥራን በማጓተት፣
ምክንያት መደርደሩ ዝምብሎ በሐሰት ።
የሰውን ሀብት መውሰድ የማይገባን ጥቅም፣
ይሄ አይደለም ወይ የሙስና ትርጉም?፣
ብዙ ነው መከራው አይነቱመም አያልቅም ።
ብዙ ወንጀሎችን በክፋት የያዘ፣
ሀገርን ያደቃል እያደነዘዘ።
ይህ ክፉ ደዌ ግን፡ ለአንዱ ብቻ አይተርፍም፣
ካልጠፋ በስተቀር፡ እርሱ አይተኛልንም፤
ስለዚህ እንነሳ፡ በጋራ እንዝመት፣
ከሥር መሠረቱ፡ ከሀገር ለማጥፋት።

ከፈቃዱ በላይ